የክስ መሰማት ሂደት

የቀጠለ...

የክስ መሰማት ሂደቱ በፍትሐብሄር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ተደንግጎ ይገኛል።

- ቀዳሚው ክፍል የመጀመሪያ ክስ ሲከፈት ስለሚፈጸም ሥነ-ሥርዐት የሚመለከት ሲሆን ይህም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 241-256 ባሉት ድንጋጌዎች ተደንግጎ የሚገኘው ነው።
- ስለክስ መሰማት የሚመለከተው ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ክርክር ስለሚሰማበትና ምስክሮች ስለሚመረመሩበት ሂደት የሚመለከት ሲሆን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 256-273 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች የሚያካትት ነው።

1.1 የመጀመሪያ ክስ ሲከፈት ስለሚፈጸም ሥነ-ሥርዐት

ከሥነ-ሥርዐት ሕጉ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ለመረዳት እንደሚቻለው የመጀመሪያ ክስ ሲከፈት የሚፈጸመው ሥነ-ሥርዓት ከክርክሩ መሰማት ሂደት በፊት መጠናቀቅ የሚገባቸው ነገሮች የሚከናወኑበትና ሌሎች ለክርክሩ መሰማት አመራር የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች የሚፈጸሙበት አግባብ ነው። ይህም የክስ መሰማት ደረጃ ሶስት ዋና ዋና ክፍሎችን የሚያካትት ሲሆን ይሄውም

- ተከራካሪዎች የሚመረመሩበት፣
- የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ብይን የሚሰጥበት እንዲሁም
- ለክርክሩ አወሳሰን መሰረታዊ ናቸው የሚባሉ ጭብጦች የሚመሰረቱበት ሂደቶች ናቸው።

1.1.1 ተከራካሪዎችን ስለመመርመር

ፍ/ቤቱ ክሱን ለመስማት በሰጠው የመጀመሪያ ቀነ ቀጠሮ የተለያዩ ተግባራት የሚከናወኑበት ሲሆን ከነዚህም መካከል፡-

- የመጀመሪያው ፍ/ቤቱ ሊያከናውን የሚገባው ነገር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 241(1) መሰረት ባለጉዳዮቹ ራሳቸው ቀርበው እንደሆነ የሚያረጋግጥበት አግባብ ነው።

እዚህ ላይ ራሳቸው ባለጉዳዮቹ የሚለው የግድ የክርክሩ ባለቤቶች ማለት ብቻ ሳይሆን እንደነገሩ ሁኔታ እነዚህኑ ተከራካሪ ወገኖችን በመወከል በነገረ-ፈጅነት ወይም በጥብቅና ወይም የሥነ-ሥርዓት ሕጉ በሚያስቀምጠው ሌላ ማንኛውም አግባብ ፍ/ቤት አንድን ሰው ወክሎ ለመቆም የሚያበቃ ውክልና ያለውን ሰው ሁሉ የሚጨምር እንደሆነ የዚህኑ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (2) እና (3) በመመልከት ለመገንዘብ ይቻላል። ይህም አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት በሀሰት ተከራካሪ ወገኑ እኔነኝ በማለትና ክርክሩን እንዳያደናቅፍ/እንዳያበላሽ እንዲሁም ያልቀረቡ ተከራካሪ ወገኖችን መብቶች ጥበቃ ለማድረግ በማሰብ ነው።

የቀጠለ...

- ፍ/ቤቱ የባለጉዳዮቹን ማንነት ካረጋገጠ በኋላ ቀጣዩ ስራው የሚሆነው የግራ ቀኙን አቤቱታ በማንበብ በአንደኛው ተከራካሪ ወገን አቤቱታ የተነሳውን የመከራከሪያ ፍሬ ነገር ሌላኛው ተከራካሪ ወገን በግልጽ ወይም በነገሩ አካባቢ ሁኔታ ያለመነውን ወይም የካደውን ነገር ያምን ወይም ይክድ እንደሆነ በመጠየቅ ተከራካሪ ወገኖችን የሚመረምርበት አግባብ ነው፤፣

የሥነ-ሥርዐት ሕጉ ቁጥር 241(1) የአማርኛው ቅጂ ፍ/ቤቱ የተከሳሹን መልስ ብቻ የሚያነብ እንደሆነና ተከሳሹን የተከሰሰበትንና በመልሱ ላይ በቀጥታ ወይም በነገሩ አካባቢ ሁኔታ እንደተካደ የሚቆጠረውን ነገር የሚያምን ወይም የሚክድ መሆኑን የሚጠይቀው እንደሆነ የሚደነግግ ቢሆንም የዚሁ ሕግ ተመሳሳይ ድንጋጌ የእንግሊዝኛ ቅጂ ግን ከዚህ በተለየ ሁኔታ፡-

የቀጠለ...

“...the court shall... read the pleadings and ascertain from each party or his pleader whether he admits or denies such allegations of fact as are made in the statement of the other party and as are not expressly or by necessary implication admitted or denied by the party against whom they ar made” በዚህም የግራ ቀኙ አቤቱታ እንደሚነበብና በአንደኛው ተከራካሪ ወገን አቤቱታ የተነሳውን የመከራከሪያ ፍሬ ነገር ሌላኛው ተከራካሪ ወገን በግልጽ ወይም በነገሩ አካባቢ ሁኔታ ያላመነውን ወይም የካደውን ነገር ያምን ወይም ይክድ እንደሆነ ይጠይቀዋል በሚል ይደነግጋል።

የቀጠለ...

ተከሳሹ ብቻ ሳይሆን ተከሳሹ ባቀረበው የጽሁፍ መልስ ላይ ያነሳቸውን መከራከሪያዎች ፍ/ቤቱ ከሳሽ ያምን ወይም ይክድ እንደሆነ መጠየቁ የሚኖረው ጠቀሜታ ተከሳሹ በመከላከያ መልሱ ላይ የሚያቀርባቸው የመከራከሪያ ፍሬ ነገሮች በከሳሽ መታመን ወይም መካዳቸው አከራካሪውን ነገር በመለየት ተገቢውን ጭብጥ ለመመስረትና ትክክለኛውን ውሳኔ ፍ/ቤቱ መስጠት እንዲችል የራሱ የሆነ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ስለሚኖረው ነው።

ይህንንም በምሳሌ ለመመልከት ያህል ከሳሽ ተከሳሽ የተበደረውን 10,000 ብር ይክፈለኝ ብሎ ላቀረበው ክስ ተከሳሽ በሰጠው የጽሁፍ መልስ ከከሳሽ 10,000 ብር ተበደሮ እንደነበረ ነገር ግን 5000 ብር ለከሳሽ ቀደም ሲል የከፈለ በመሆኑ ልከፍል የሚገባው 5,000 ብር እንጂ 10,000 ብር ሊሆን አይገባም በሚል መከራከሪያ ቢያቀርብ በዚህ መከራከሪያ ላይ ከሳሽ ሲጠየቅ የሚሰጠው ምላሽ ተገቢውን ጭብጥ ለመያዝ ከሚኖረው ፋይዳ በተጨማሪ የትኛው ተከራካሪ ወገን የማስረዳት ሸክም አለበት የሚለውን ለመለየትም የሚኖረው ጥቅም ከፍተኛ ነው።

የቀጠለ...

በዚህ ጉዳይ ላይ ከሳሽ ለምሳሌ ምንም አይነት ብር ተከሳሽ አልከፈለኝም በሚል ምላሽ ቢሰጥ በመጀመሪያ የክርክሩ ጭብጥ ተከሳሽ ለከሳሽ 5,000 ብር ከፍሎታል ወይስ አልከፈለውም የሚል ሲሆን የማስረዳት ሸክሙም ከከሳሽ ወደተከሳሽ የሚዞር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በመሆኑም ከአማርኛው ቅጂ ይልቅ የእንግሊዝኛው ቅጂ በተሻለ ክርክሩን ለመምራት የሚያስችል እንደሆነ መመልከት ይቻላል።

- በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 241(2) መሰረት ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን ጉዳዮች ወይም ሌሎች ነገሮች አብራርቶ ለማስረዳት ጠቃሚና ተገቢ መስሎ በገመተው ዘዴ የቃል ጥያቄ በማቅረብ ሊመረምራቸው የሚችል ሲሆን ከግራ ቀኙ አንዱ ሌላኛው ወገን ሊያብራራለት የሚፈልገው ጥያቄ ያለው እንደሆነ ይህንኑ በፍ/ቤቱ በኩል ጥያቄው እንዲቀርብና እንዲብራራለት ማድረግ ይችላል። ከዚህም ለመረዳት የሚቻለው ግራ ቀኙ በቀጥታ የቃል ክርክር እንዲያደርጉ የሚፈቀድ አለመሆኑን ነው።

የቀጠለ...

በዚሁ አግባብ ፍ/ቤቱ ተከራካሪ ወገኖችን በሚመረምርበት ጊዜ ፍ/ቤቱ ወይም በፍ/ቤቱ በኩል ከሌላኛው ተከራካሪ ወገን የሚነሱለትን ለክርክሩ ማብራሪያ የሚሆኑትን ማንኛዎቹንም ነገሮች የባለጉዳዩ ነገረ-ፈጅ ወይም ጠበቃ ለማስረዳት ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ ወይም ለቀረበለት ጥያቄ ተገቢውን መልስ ለመስጠት የማይችል የሆነ እንደሆነና ፍ/ቤቱ ራሱ ባለጉዳዩ ለቀረበለት ጥያቄ መልስ ለመስጠት የሚገባው መሆኑን ወይም ለሚቀርብለት ጥያቄ መልስ ለመስጠት የሚችል መሆኑን ሲረዳው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 241(3) መሰረት ተለዋጭ ቀነ ቀጠሮ በመስጠት ራሱ ባለጉዳዩ እንዲቀረብ ለማዘዝ ይችላል።

ይህም የሕጉ አቀራረጽ በፍ/ቤት በሚደረግ ክርክር ተከራካሪ ወገኖች በፍ/ቤቱ ወይም ከሌላኛው ተከራካሪ ወገን ለሚነሳላቸው ጥያቄ ምላሽ ባይሰጡም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 83 እና 235(2) ድንጋጌዎች በቀጥታ ተፈጻሚ በመሆን እንዳመኑ የሚቆጠር አለመሆኑን ነው፣

የቀጠለ...

በአጠቃላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 241 መሰረት ተከራካሪ ወገኖች በቀጥታ የሚከራከሩበት አግባብ የሌለ መሆኑንና ፍ/ቤቱ ራሱ መብራራት የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች የቀረቡትን የጽሁፍ አቤቱታዎች መሰረት በማድረግ ለተከራካሪ ወገኖቹ ጥያቄ እያቀረበ ነገሩን የሚያጠራበት የክስ መሰማት ደረጃ ነው። ይሁንና ፍ/ቤቶች በተግባር እንደሚታየው ብዙ ጊዜ በአቤቱታዎቹ ይዘት ተገቢውን ዝግጅት ባለማድረግ ይሁን ሕጉን በአግባቡ ባለመረዳት ለግራ ቀኙ መብራራት የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ከመጠየቅና ከመረዳት ይልቅ ከሳሽ ተከሳሹ በጽሁፍ አቤቱታቸው ላይ ያቀረቡትን ክስና መልስ እንደገና ለፍ/ቤቱ በችሎት የሚያስገለብጡበት አሰራር የዳበረ ሆኖ ይገኛል።

ይህም አሰራር የፍ/ቤቱንና የተከራካሪ ወገኖችን ጊዜና ጉልበት ከማጥፋት ባለፈ ለጉዳዩ አወሳሰን የሚፈይደው ነገር የለም። ከዚህ በተለየ በአንድ አንድ ፍ/ቤቶች ደግሞ ግራ ቀኙን ከጽሁፍ መልሳቸሁ የተለየ ነገር ካላቸሁ በማለት አዲስ ነገር እንዲያቀርቡ እድል የሚሰጡበት ሁኔታ ይስተዋላል። ይሁንና ይህ አይነቱ አሰራር በሥነ-ሥርዓት ሕጉ በዚህ አግባብ እንዲቀርብ የማይፈቅደውን አዲስ ነገር እንዲቀርብ በማድረግ የክርክሩ ሂደት እንዲንዛዛ የማድረግ እንዲሁም በተከራካሪ ወገኖች መብት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊፈጥር የሚችል በመሆኑ እንዲህ አይነቱ ከሕጉ የወጣ አሰራር ሊታረም ይገባል።

የቀጠለ...

ፍ/ቤቱ ተከራካሪ ወገኖችን መርምሮ ካጠናቀቀ በኋላ እንደነገሩ ሁኔታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 242 መሰረት ፍርድ ሊሰጥ ይችላል። ይህም ሊሆን የሚችለው አንደኛው ተከራካሪ ወገን በአቤቱታው ወይም በጽሁፍ ወይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 241 መሰረት በተደረገው የፍ/ቤቱ ምርመራ ጊዜ የታመነ ነገር ያለ እንደሆነ ነው። በፍትሐብሔር ጉዳይ አንድ ጉዳይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ሊታመን ይችላል።

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 242 ድንጋጌ መንፈስ እምነትን መሰረት አድርጎ ፍርድ ሊሠጥ የሚችለው በቀጥታ በታመኑ ነገሮች ላይ እንደሆነ በተለይም "በመከላከያ መልሱ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የተከሰሰበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል የሚያምን መሆኑን የገለጸ እንደሆነ" ከሚለው አገላለጽ ለመገንዘብ ይቻላል። ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት በሕጉ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ እንደታመኑ የሚቆጠሩ ነገሮች ላይ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 235(2) መሰረት እንደነገሩ ሁኔታ ማስረጃ እንዲሰማባቸው ለማዘዝ የሚችል በመሆኑ እንዳለቀለት ጉዳይ የሚቆጠር ባለመሆኑ ነው።

የቀጠለ...

ስለሆነም በቀጥታ በማመልከቻው ወይም በሌላ ማንኛውም ጽሁፍ ወይም በፍ/ቤቱ ምርመራ የታመኑ ነገሮች ሲኖሩ የእምነቱ ተጠቃሚ የሆነው ወገን በታመነው መሰረት ፍርድ ይሰጠኝ ብሎ ካመለከተ ሌሎች ጉዳዮች በምስክር የሚጣሩ ቢኖሩም ፍ/ቤቱ ይህንኑ ፍርድ ሊሰጥ ይገባል።

ከዚህም በተጨማሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 242 በተመለከተው አግባብ ፍ/ቤቱ የእምነት ቃል ያልተሰጠበትን ማንኛውንም ነገር ወይም ጽሑፍ እምነት ክደት እንዲሰጥበት በየትኛውም የክርክሩ ደረጃ እየጠየቀ በሚሰጠው መልስ ላይ የሚታመን ነገር ካለ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 242 መሰረት ተገቢውን ፍርድ ለመስጠት የሚከለክለው ነገር የሌለ እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ / 243 ላይ ተደንግጓል።

1.1.2. የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች

ከእምነት ቃል በመቀጠል በአንድ ፍ/ቤት እየታየ ያለ ጉዳይ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ሊቋጭ ይችላል። እነዚህ መቃወሚያዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 244(2) እንዲሁም በልዩ ልዩ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ድንጋጌዎች ላይ ተመልክተው ይገኛሉ። ፍ/ቤቱ የነገሩን ጭብጥ ከመያዙ እንዲሁም ማስረጃ ተቀብሎ ከመመርመሩ ወይም ምስክሮችን ከመስማቱ አስቀድሞ የቀረቡ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል።

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 244(2) ከተዘረዘሩት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች መካከል አንዱ የፍ/ቤት ሥልጣን አለመኖር ነው። ፍ/ቤቱ ጉዳዩን ለማየት ከሶስቱ የፍ/ቤት የሥልጣን አይነቶች አንዱ እንኳ የሌለው እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 231 መሰረት የክሱን መዝገብ መዝጋት ይኖርበታል። ይሁንና በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ፍ/ቤቱ ይህንን ሀላፊነቱን ያልተወጣ እንደሆነ ተከሳሹ ፍ/ቤቱ የቀረበለትን ጉዳይ ለማየት የሚያስችል ሥልጣን እንደሌለው በመግለጽ መቃወሚያውን ለማቅረብ ይችላል።

የቀጠለ...

ሌላው በሕጉ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የተመለከተው ክስ የቀረበበት ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ የተወሰነ መሆኑ ነው። አንድ ጉዳይ ቀደም ሲል በፍርድ ያለቀ ነው በሚል መቃወሚያ ለማቅረብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 5 ላይ የተመለከቱት ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላታቸው ሊረጋገጥ የሚገባ ነው። በዚህ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (1) መሰረት፦-

“በህግ ስልጣን የተሰጠው ማንኛውም ፍርድ ቤት ክርክሩን ተቀብሎ የመጨረሻ የፍርድ ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ቀድሞ በፍርድ የተወሰነው ክርክር ስረ-ነገርና የተያዘው ጭብጥ አንድ ዓይነት ከሆነ በክርክሩ ላይ የነበሩት ወይም ከተከራካሪዎቹ መብት ያገኙ ሶስተኛ ወገኖች በዚያው ነገር ሁለተኛ ክስ ወይም ማናቸውንም አይነት ሌላ ክርክር ለማቅረብ አይችሉም” በማለት ይደነግጋል።

የቀጠለ...

ከዚህ ንዑስ አንቀጽ የአማርኛው ቅጂ ለመረዳት እንደሚቻለው አንድ ክርክር በፍርድ አልቋል ለማለት ክርክሩ በህግ ስልጣን በተሰጠው ፍ/ቤት ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑ፣ ውሳኔው የመጨረሻ መሆኑ፣ የክርክሩ ስረ-ነገርና ጭብጡ ተመሳሳይ መሆኑ እንዲሁም ተከራካሪዎቹና ከእነርሱ መብት ያገኙ ሶስተኛ ወገኖች ተመሳሳይ መሆናቸው መሟላት የሚገባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች እንደሆኑ ለመረዳት ይቻላል።

ከአማርኛው ቅጂ በተለየ ሁኔታ ግን የእንግሊዝኛው ቅጂ፡-

“No court shall try any suit or issue in which the matter directly and substantially in issue has been directly and substantially in issue in a former suit between the same parties, or between parties under whom they or any of them claim, litigating under the same title, and has been heard and finally decided.” በሚል የተቀመጠ ሲሆን በዚህም መሰረት፡-

የቀጠለ...

ማንኛውም ፍ/ቤት ቀደም ሲል ውሳኔ ያረፈበትን አንድ ጉዳይ መዳኘት አይችልም ከማለት ውጪ ልክ እንደአማርኛው ቅጂ ቀደም ሲል ውሳኔ ያረፈበት ክስ ስልጣን ባለው ፍ/ቤት ታይቶ መሆንን በመስፈርትነት አያስቀምጥም።

ከሁለቱ ቅጂዎች የትኛው ቅጂ ተፈጻሚ ሊሆን ይገባል? የሚለውን ለመመለስ ሌሎች የስነ-ስርዓት ህጉን ድንጋጌዎች መመርመሩ ጠቃሚ ይሆናል። በዚህ ረገድ የዚሁ ህግ ቁጥር 212 እንደሚደነግገው በአንድ ፍ/ቤት የተሰጠ አንድ ውሳኔ፣ ቀደም ሲል በእንግሊዝኛው ቅጂ ባየነው አግባብ፣ በይግባኝ እስካልተሻረ ድረስ በህግ ፊት የጸና እንደሚሆንና በኢትዮጵያ በህግ ፊት የማይጸና ወይም ፍርስ (null and void) የሚባል ውሳኔ እንደሌለ በግልጽ ደንግጓል።

በዚህም መሰረት በሕግ ሥልጣን በተሠጠው ፍ/ቤት ውሳኔ ያገኘ የሚለው ቅድመ-ሁኔታ በፍርድ የመጨረሻ ውሳኔ የማለቅ መርህ ላይ ተፈጻሚነት የሚኖረው አይሆንም።

የቀጠለ...

የውሳኔው የመጨረሻነት በፍርድ የማለቅ መርህ ተፈጻሚ እንዲሆን ወሳኝ ቅድመ-ሁኔታ ሲሆን በዚህም ቀደም ሲል የተሰጠው ውሳኔ በፍሬ-ነገሩ ላይ የተሰጠ መሆኑ እንደሆነ ከልዩ ልዩ የስነ-ስርዓት ህጉ ድንጋጌዎች ምንባብ ለመገንዘብ ይቻላል። ከዚህ አንጻር ለምሳሌ ብንመለከት፣

መጥሪያ ባግባቡ ባለማድረሱ ምክንያት መዝገቡ በህጉ አንቀጽ 70(መ) መሰረት የተዘጋበት ከሳሽ ክሱን በሌላ ጊዜ እንደአዲስ ቢያቀርብ ወይም

አንድ ፍ/ቤት የቀረበው ክስ ከስልጣኔ በላይ ነው በሚል መዝገቡን በህጉ አንቀጽ 244(2)(ሀ) መሰረት ቢዘጋውና መዝገቡ የተዘጋበት ከሳሽ ክሱን ለመመልከት ስልጣኑ ለሚፈቅድለት ፍ/ቤት በሌላ ጊዜ ክሱን ቢያቀርብ፣ ይኸው የፍ/ቤቱ ውሳኔ በፍሬ-ነገሩ ላይ ስላልሆነ ውሳኔው የመጨረሻ ነው በማለት በፍርድ የማለቅ መርህ ተፈጻሚ ሊሆንበት አይችልም።

የቀጠለ...

በመሆኑም በፍርድ የማለቅ መርህ ተፈጻሚነት እንዲኖረው ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት በፍሬ-ነገሩ ላይ ውሳኔ በመስጠት በጉዳዩ ላይ በድጋሚ ክርክር እንዳይነሳ አድርጎ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠ እንደሆነ ነው።

“ቀድሞ በፍርድ የተወሰነው ክርክር ስረ-ነገርና የተያዘው ጭብጥ አንድ አይነት ከሆነ” የሚለው ሌላው ቅድመ-ሁኔታ ወሰኑ እስከምን ድረስ ነው? የሚለውን በተመለከተ በፍርድ የማለቅ መርህ ቀደም ሲል በውሳኔ ያለቀን ጉዳይ ወይም ነገር በድጋሚ እንዳይቀርብ መከልከልን “claim preclusion’’ እና በአንድ ክርክር በመከራከሪያነት ተነስቶ ውሳኔ ሊያርፍበት ይገባ የነበረን ነገር በድጋሚ በሌላ ክርክር እንዳይነሳ የሚከለክልበት አግባብ “issue preclusion’’ የሚባሉ ሁለት የተዛመዱ ጽንሰ ሀሳቦችን አካቶ የያዘ መርህ ነው።

የቀጠለ...

በመሆኑም በውሳኔ ያለቀው የስረ-ነገርና ጭብጥ አንድ አይነት መሆን ወሰን ቀደም ባለ ክርክር ተነስተው ውሳኔ ባረፈባቸው ስረ-ነገርና ጭብጥ ላይ ሳይወሰን በመከራከሪያነት ሊነሱ ይገቡ የነበሩ ነገሮችን ሁሉ እንደሚያካትት መገንዘብ ይቻላል።

ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 5(1) እና (2) ለመመልከት እንደሚቻለው ሁለቱም ጽንሰ-ሀሳቦች ተካተው የሚገኙ እንደሆነ ነው። ከፍ ሲል በአንቀጽ 5(1) ለማየት እንደተሞከረው..." ቀድሞ በፍርድ የተወሰነው ክርክር ስረ-ነገርና የተያዘው ጭብጥ አንድ አይነት ከሆነ"... በተመሳሳይ ስረ-ነገር ወይም ጭብጥ ላይ ሌላ ማናቸውንም ክርክር በድጋሚ ማቅረብ እንደማይቻል ደንግጓል። ይህም በግልጽ የሚያመለክተው፣ ቀደም ባለ ክስ በተከራካሪዎች ክርክር ተደርጎባቸውና በውሳኔ ያለቁ ነገሮችን መሰረት በማድረግ በድጋሚ ክርክር ማቅረብ አይቻልም የሚለውን ጽንሰ-ሀሳብ ነው።

የቀጠለ...

በሌላ በኩል፣ የዚሁ ድንጋጌ ንኡስ ቁጥር (2) በግልጽ “በቀድሞው ክርክር ላይ የማስረጃ ወይም የመከላከያ ወይም የመቃወሚያ መሰረት መሆን ይገባቸው ነበር ወይም ለመሆን ይችሉ ነበር የሚባሉት ነገሮችና ምክንያቶች ሁሉ ለስረ-ነገሩ መሰረት በመሆን ከቀድሞው ውሳኔ ጋር ተቀላቅለው እንዳለቁ የሚቆጠሩ ናቸው” በሚል ደንግጓል። ይህም በአንድ ክርክር በመከራከሪያነት ተነስቶ ውሳኔ ሊያርፍበት ይገባ የነበረን ነገር በድጋሚ በሌላ ክርክር እንዳይነሳ የሚከለክልበት አግባብ እንደሆነ ማየት ይቻላል።

የቀጠለ...

በአፈጻጸም ረገድ የመከላከያ ወይም የመቃወሚያ ወይም የማስረጃ መሰረት በመሆን ቀደም ባለው ክርክር ተነስተው ውሳኔ ሊያርፍባቸው ይገባ ነበር የሚባሉ ነገሮች ምን አይነት ነገሮች እንደሆኑ ህጉ በግልጽ የሚያስቀምጠው ነገር የለም። ይህም በመሆኑ ምክንያት በፍ/ቤቶች መካከል በተመሳሳይ ህጉን በመተርጎም ረገድ ልዩነት ሊኖር ይችላል።

እዚህ ላይ በትኩረት መታየት የሚገባው ነገር በአንቀጽ 5(2) የተመለከተው "ለስረ-ነገሩ መሰረት በመሆን" የሚለው አገላለጽ ነው። ከዚህ አገላለጽ ለመረዳት እንደሚቻለው ለክርክሩ መነሻ ከሆነው ስረ-ነገር ውጪ ራሱን ችሎ የስረ-ነገር ምክንያት በመሆን እንደአዲስ በመቅረብ መከራከሪያ ለመሆን የማይችል የመቃወሚያ ወይም የመከላከያ ወይም የማስረጃ መሰረቶችን የሚመለከት መሆኑን ነው።

የቀጠለ...

ለምሳሌ፡- ተከሳሽ ከከሳሽ ጋር በገባው የእቃ አቅርቦት ውል እንደውሉ ባለመፈጸሙ በቀረበበት ክስ የተለያዩ መከራከሪያዎችን በማቅረብ ቢከራከርም ጉዳዩን የሚያየው ፍ/ቤት የተከሳሽን መከራከሪያዎች ባለመቀበል ከሳሽ፣ ተከሳሽ እንደውሉ ባለመፈጸሙ ምክንያት፣ ለደረሰበት ኪሳራ ሀላፊ እንደሆነ በመግለጽ ውሳኔ በመስጠት መዝገቡን ይዘጋል። ነገር ግን ተከሳሽ ውሉን ባግባቡ ያልፈጸመው በአስገዳጅ ምክንያት ቢሆንና ይህንኑ ምክንያት ተከሳሽ በመከላከያነት ያላቀረበው እንደሆነ እንደ አዲስ ራሱን ችሎ የሰረ-ነገር መነሻ በመሆን መከራከሪያ ለመሆን ስለማይችል ቀደም ብሎ ውሳኔ በማግኘት ካለቀው ጉዳይ ጋር ተቀላቅሎ እንዳለቀ ይቆጠራል ማለት ነው። ሌላው በፍርድ የማለቅ መርህ የሚኖረውን የተፈጻሚነት ወሰን በአንቀጽ 5(3) ላይ የተመለከተው ሲሆን በዚህም መሰረት በቀድሞው ክርክርና ሙግት ላይ በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆበት ጥያቄው ተቀባይነትን ሳያገኝ የታለፈ እንደሆነ በዚህ ቁጥር አግባብ የተጠየቀው ዳኝነት እንደተከለከለ የሚቆጠር መሆኑ ነው።

የቀጠለ...

በፍርድ የማለቅ መርህ ከተከራካሪ ወገኖች አንጻር በሶስት አይነት ሰዎች ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ሲሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 5(1)መሰረት የመጀመሪያው ውሳኔ ባገኘ አንድ ጉዳይ ላይ በተከራካሪነት ተካፋይ በሆኑ ሰዎች ላይ እንዲሁም

በሁለተኛ ደረጃ በአንድ ክርክር ተሳታፊ ከነበሩ ተከራካሪዎች በስጦታ፣ በውርስ እና በሽያጭ መብት ያገኙ ሶስተኛ ወገኖች ላይ ሲሆን፣

በአንቀጽ 5(4) ላይ የተገለጸው ሁኔታ ማለትም ማህበራዊ ወይም ግላዊ መብትን መሰረት በማድረግ ብዙ ሰዎች በቅን ልቦና ክስ በመመስረት ባደረጉት ክርክር፣ ክርክሩ በተደረገበት ጉዳይ ላይ መብት ያላቸው ሰዎች በክርክሩ ተካፋይ ባይሆኑም በጉዳዩ ላይ በተሰጠው ውሳኔ ተገዢ የሚሆኑበት አግባብ ሶስተኛው መርሁ ተፈጻሚ የሚሆንባቸው ሰዎች ናቸው።

ክስ የቀረበበት ጉዳይ በሌላ ፍርድ ቤት ቀርቦ በክርክር ላይ ያለ መሆኑን በተመለከተ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 7(1) ላይ እንደተደነገገው አንድ የፍትሐ ብሔር ክስ የሚታየው በአንድ የፍትሐብሔር ፍ/ቤት ብቻ ነው።

የቀጠለ...

በዚህም መሰረት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 8(1) ላይ እንደተመለከተው “ለክርክሩ መነሻ የሆነው ነገር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ ለውሳኔም የቀረበው ጭብጥ ሥረ-ነገሩ አንድ ሲሆን እንዲሁም ተከራካሪዎቹ ወገኖች አንድ ወይም ተመሳሳይ ሲሆኑና ክሱም ለባለ ሥልጣኑ ፍርድ ቤት ቀርቦ በመሰማት ላይ ሆኖ በቀጠሮ ላይ የሚገኘውን የፍትሐብሔር ክርክር ሌላው ፍርድ ቤት ተቀብሎ ለማከራከር አይችልም። እንዲሁም ሌሎቹ ወገኖች ከዋናዎቹ ተከራካሪዎች ላይ መብት አለን በማለት በዚሁ ክርክር በቀረበበት በአንዱ ነገር ላይ በሌላ ፍርድ ቤት ክስ ለማቅረብ አይችሉም።” በሚል ተደንግጓል።

የቀጠለ...

ክስ የቀረበበት ጉዳይ በሌላ ፍርድ ቤት ቀርቦ በክርክር ላይ ያለ ነው ለማለት በዋናነት ሶስት ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል። እነዚህም፡-

- ለክርክሩ መነሻ የሆነው ነገር አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይነት ያለው ሆኖ ለውሳኔም የቀረበው ጭብጥ ሥረ-ነገሩ አንድ አይነት መሆኑ፣
- ተከራካሪ ወገኖቹ አንድ አይነት ወይም ተመሳሳይ ሲሆኑ እንዲሁም
- ጉዳዩ የቀረበው ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት የሆነ እንደሆነ የሚሉት ናቸው።

ከተከራካሪ ወገኖች አንጻር ከዋናዎቹ ባለጉዳዮች በተጨማሪ ከነሱ መብት አለን የሚሉ ሌሎች ሰዎችም ቢሆኑ ዋናዎቹ ባለጉዳዮች ካቀረቡበት ፍ/ቤት ውጪ በሌላ ፍ/ቤት ለማቅረብ የሚችሉ አይሆኑም።

የቀጠለ...

አንድ ጉዳይ ቀደም ሲል በአንድ ፍ/ቤት ቀርቦ እየታየ መሆን ያንኑ ተመሳሳይ ጉዳይ ሌላ ፍ/ቤት ከመቀበል የማይከለክሉ ሁለት ልዩ ሁኔታዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 8 (1) እና (2) ላይ ተመልክተው ይገኛሉ። ከነዚህ ልዩ ሁኔታዎች መካከል የመጀመሪያው፣

- ቀደም ሲል የቀረበው ጉዳይ ሥልጣን በሌለው ፍ/ቤት የሆነ እንደሆነ ነው።
- ሌላው ልዩ ሁኔታ አንድ ጉዳይ የቀረበው በውጪ ሀገር ፍ/ቤት ከሆነ ያንኑ ተመሳሳይ ጉዳይ በኢትዮጵያ የሚገኝ ፍ/ቤት ከመዳኘት የሚከለክለው ነገር አይኖርም።
- ሌላው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244(2) ላይ የተመለከተው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክሱ በሽምግልና ታይቶ በስምምነት የተፈጸመ መሆኑ ወይም ለእርቅ የተቀጠረ መሆኑ የሚለው ነው።

የቀጠለ...

አከራካሪው ነገር በሽምግልና ሊታይ እንደማይችል በሕግ ክልከላ እስካልተደረገበት ድረስ ተከራካሪ ወገኖች በነገሩ ላይ ወደፊት ክርክር ቢነሳ ጉዳያችንን በሽምግልና እንጨርሳለን በሚል ስምምነት ለማድረግ የሚችሉ መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 315(1) ይደነግጋል።

በዚህም መሰረት ፍ/ቤት የቀረበው ጉዳይ ቀደም ሲል ተከራካሪ ወገኖች እንዲህ አይነት ስምምነት አድርገው ከሆነ ይህንኑ በመቃወሚያነት ለማንሳት የሚችሉ ይሆናል።

የቀጠለ...

እንዲሁም ጉዳዩ በሽምግልና ውሳኔ ያገኘ ከሆነ ውሳኔ የተሰጠበት ተከራካሪ ወገን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 350-357 በተመለከቱት ድንጋጌዎች አግባብ ይግባኝ ካላቀረበ በስተቀር አዲስ ክስ ለማቅረብ የሚችል ባለመሆኑ ክሱ በሽምግልና ያለቀ ነው በሚል መቃወሚያ ለማቅረብ የሚቻል ይሆናል።

ጉዳዩን በእርቅ ለመጨረስ ባለጉዳዮቹ የተስማሙ እንደሆነና ይኄው እርቅ ፍጻሜ ሳያገኝ እንደኖው ባለጉዳይ ጉዳዩን ወደ ፍ/ቤት የወሰደው እንደሆነ ሌላኛው ባለጉዳይ ጉዳዩ ለእርቅ የተቀጠረ ነው በሚል መቃወሚያ ለማቅረብ የሚችል ይሆናል።

የቀጠለ...

ይህም በፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 3321 (3) መሰረት በእርቅ ጉዳያቸውን ለመጨረስ የተስማሙ ተዋዋይ ወገኖች የመረጡት አስታራቂ በተዋዋዮቹ ወይም በሕግ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ እርቅ ስላለመደረጉ የጽሁፍ መግለጫ እስካላዘጋጁ ድረስ ተዋዋይ ወገኖቹ በእርቅ የተያዘውን ጉዳይ ለፍ/ቤት ለማቅረብ እንደማይችሉ ተመልክቷል።

ከላይ ከ(ሀ) እስከ (መ) ድረስ ከተመለከትናቸው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚዎች በተጨማሪ፤

እንደኛው ተከራካሪ ወገን በነገሩ የማያገባው መሆኑን፣ ክሱ በይርጋ የሚታገድ መሆኑን እንዲሁም በሕግ ቅድሚያ የመከሰስ ፍቃድ የሚያስፈልግ ሲሆንና ፍቃድ ሳያገኝ የቀረበ ክስ ከሆነ የሚሉት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 244(2) የተመለከቱ ሌሎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ናቸው።

የቀጠለ...

ከነዚህም በተጨማሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕጉ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ተመልክተው ይገኛሉ። ከነዚህም መካከል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 39(2)፣ 216(3) እና (4)፣ 220፣ 250 እንዲሁም 279 (1) የሚጠቀሱ ናቸው።

የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች በመርህ ደረጃ በቶሎ መቅረብ ያለባቸው እንደሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 244(3) ላይ ተደንግጓል። በቶሎ ያልቀረቡ መቃወሚያዎች በልዩ ሁኔታ ትክክለኛ ፍርድን ለመስጠት የሚያሰናክሉ ሆነው ካልተገኙ በስተቀር ባለጉዳዩ ራሱ ሆነ ብሎ ለማቅረብ ባለመፈለግ እንደተዋቸው ይቆጠራሉ።

ትክክለኛ ፍርድን ለመስጠት የሚያሰናክሉ መቃወሚያዎች ከሆኑ በየትኛውም የክርክሩ ደረጃ በፍ/ቤቱ ወይም በተከራካሪ ወገኖች ሊነሱ የሚችሉ ይሆናል።

የቀጠለ...

እዚህ ላይ ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ ከተመለከቱት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች መካከል ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት የሚያሰናክሉ የሚባሉት የትኞቹ መቃወሚያዎች ናቸው? የሚለው ነው።

በዚህ ረገድ በሕጉ በግልጽ ትክክለኛ ፍርድን ለመስጠት የሚያሰናክል እንደሆነ የተመለከተው መቃወሚያ ፍ/ቤቱ የስረ-ነገር ሥልጣን የሌለው መሆኑ ሲሆን ይህም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 10(2) እንደሚደነግገው "በዚህ ሕግ በቁጥር 244 በተነገረሙ መሠረት ስለ ፍርድ ቤቱ የዳኝነት ሥልጣን ማናቸውም ተከራካሪ ወገን መቃወሚያ ባያቀርብም እንኳ በቁጥር 245 ድንጋጌ መሠረት የክሱ ማመልከቻ ተቀባይነት የለውም ብሎ ራሱ መመለስ አለበት።" ከስረ-ነገር ሥልጣን አለመኖር ውጪ ባሉት መቃወሚያዎች ግን ሕጉ ምንም የሚለው ነገር የለም።

በቀጠሮ ላይ የሚገኙ ክሶች ከአንድ በላይ በሆነ ፍ/ቤት ሊቀርቡና ሊታዩ ሰለማይችሉ እንዲሁም በአንድ ጉዳይ ላይ ከአንድ በላይ የሆኑ ፍ/ቤቶች ውሳኔ ቢሰጡባቸው ለማስፈጸም አስቸጋሪ በመሆኑ ፍርድን የሚያሰናክል እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል።

የቀጠለ...

ከመቃወሚያዎቹ መካከል አንዱ የሆነው በፍርድ የመጨረሻ ውሳኔ የማለቅ መርህ መነሻዎችን ብንመለከት መርሁ ሶስት ነገሮችን ማለትም፤

- የፍ/ቤቶችን ኢኮኖሚያዊነት፣
- በተመሳሳይ ጉዳይ ፍ/ቤቶች የሚሰጧቸው ውሳኔዎች ወጥነት እንዲኖራቸው ማድረግና
- በአንድ ጉዳይ ላይ የሚሰጥ የፍ/ቤት ውሳኔን የመጨረሻ ማድረግ ለማሳካት ታሳቢ ያደረጋቸው መነሻዎች ናቸው።

ከዚህ አንጻር አንድ ፍ/ቤት የቀረበለት ክስ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት መሆኑን በየትኛውም የክርክሩ ደረጃ ከተረዳ ወይም ተከራካሪው ወገን ይህንኑ መቃወሚያ ካነሳ ፍ/ቤቱ መቃወሚያውን መሰረት በማድረግ ክሱን በመሰረዝ ጉዳዩን መቋጨት ካልቻለ እነዚህኑ የመርሁን መነሻዎች ሊያሳካ አይችልም።

የቀጠለ...

ይህም ማለት በአንድ ጉዳይ ተመሳሳይ በሆነ የክስ ምክንያት ከአንድ በላይ ክስ እንዲቀርብ የሚፈቀድ ከሆነ ከፍ/ቤት ኢኮኖሚያዊነት በተቃረነ መልኩ የፍ/ቤቱንና የተከራካሪ ወገኖችን ጊዜ፣ ጉልበትና ወጪ ከፍ እንዲል (ያላግባብ እንዲባክን) ያደርጋል፤

እንዲሁም በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ወጥነት ያለው ውሳኔ እንዳይኖር እድል ከመፍጠሩም ባለፈ ቀደም ብሎ ከተሰጠው ውሳኔ ተቃራኒ የሆነ ውሳኔ በመስጠት በውሳኔዎች አፈጻጸም ላይ አስቸጋሪ ሁኔታ እንዲፈጠር፤

ብሎም የፍ/ቤቶችን ተአማኒነትና ተገማችነት ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ ያደርጋል።

በመሆኑም ለመርሁ መነሻ ከሆኑ ሀሳቦች ለመረዳት እንደሚቻለው የመርሁ አላማ ትክክለኛ ፍርድን ማሳካት መሆኑን ነው። “ትክክለኛ ፍርድ” የሚለው የተለያዩ ነገሮችን ሊመለከት የሚችል ሲሆን በተለይም፥-

የቀጠለ...

የሚሰጠው ውሳኔ ሊፈጸም የሚችል መሆን አለመሆኑ አንዱ ሁኔታ ሊሆን እንደሚችል ግልጽ ነው። ከአንድ በላይ የሆኑ ውሳኔዎች እንዲኖሩ የሚፈቀድ ከሆነ ውሳኔዎቹን ለማስፈጸም ፍ/ቤቶች ራሳቸው ችግር ውስጥ የሚገቡበት ሁኔታ እንዲፈጠር ብሎም የተሰጠው ውሳኔ ቀደም ብሎ የተፈጸመና በድጋሚ ሊፈጸም የማይችል በመሆን ውሳኔው እንዲሁ ሊቀር የሚችልበትን አጋጣሚ ይፈጥራል። ይህ አይነቱ ችግር የሚመነጨው ፍርዱ ትክክለኛ ባለመሆኑ ምክንያት እንደሆነ ግልጽ ነው።

በመሆኑም ከሰረ-ነገር ሥልጣን አለመኖር በተጨማሪ በፍርድ የመጨረሻ ውሳኔ የማግኘት መርህ ትክክለኛ ፍርድ ለመስጠት ከሚያሰናክሉ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ሊመደብ የሚገባና መቃወሚያውም በየትኛውም የክርክሩ ደረጃ በተከራካሪ ወገኖች ወይም በፍ/ቤቱ ሊነሳ የሚችል አድርጎ መውሰዱ መርሁ የታሰበለትን አላማ ለማሳካት የሚያስችለው ይሆናል።

የቀጠለ...

ከነዚህ ሁለት መቃወሚያዎች በተጨማሪ ትክክለኛ ፍትህን ለመስጠት የሚያሰናክል ነው ባይባልም በሥነ-ሥርዐት ሕጉ የተመለከቱ የይርጋ ደንቦችን ተከራካሪ ወገኖች ባያነሷቸውም ፍ/ቤቱ ሊያነሳቸውና ይኄው የይርጋ ደንብ ያለፈውን ጉዳይ ውድቅ ለማድረግ የሚችል እንደሆነ የፌደራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰበር መዝገብ ቁጥር 17361 (ቅጽ 1) ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ በዚሁ አግባብ ፍ/ቤቶች የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ይርጋ በራሳቸው አነሳሽነት ለመፈጸም የሚችሉ ይሆናል።

ፍ/ቤቱ በሚቀርቡለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ላይ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን ካቀረቡ በኋላ ማስረጃ መቅረብ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ይኄው ማስረጃ እንዲቀርብ በማድረግ መቃወሚያው ትክክለኛ ሆኖ ካገኘው እንደቀረበው መቃወሚያ አይነት ሁለት አይነት ውሳኔዎች የሚሰጥ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 245(1) እና (2) የጣምራ ምንባብ ለመረዳት ይቻላል።

የቀጠለ...

በዚህም መሰረት መቃወሚያው በፍርድ የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘ መሆኑንና ክሱ በይርጋ የታገደ መሆኑን መሰረት በማድረግ የቀረበ ከሆነ ክሱ የሚዘጋ ሲሆን፣

በሌሎች መቃወሚያዎች ላይ ግን መዝገቡን የሚዘጋ ይሆናል። የመዝገብ መዘጋት በዚያው የክስ ምክንያት አዲስ ክስ ለማቅረብ የሚከለክል እንዳልሆነ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 245(3) ይደነግጋል።

1.1.3 የጭብጥ ምስረታ

ሀ. የጭብጥ ምንነትና አመሰራረት

ለፍ/ቤቱ የቀረበው ጉዳይ በተከሳሹ እምነት ወይም በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች በፍርድ ውሳኔ ወይም በብይን ያልተዘጋ እንደሆነና ተከሳሹ ነገሩ በመጀመሪያ በሚሰማበት ቀን መከላከያውን ያላቀረበ እንደሆነ ፍ/ቤቱ ለጉዳዩ አወሳሰን የሚረዱትን ጭብጦች እንደሚመሰርት ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ /246(1) እና (2) ለመረዳት ይቻላል።

ጭብጥ ማለት አንደኛው ተከራካሪ ወገን አለ ያለውን የሕግ ወይም የነገር አግባብ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን በማስተባበል የሚክደው ነገር ነው። እዚህ ላይ በትኩረት ሊታይ የሚገባው ነገር ግራ ቀኙ የተካካዱት ነገር ሁሉ ጭብጥ ሊባል እንደማይችል ነው።

የቀጠለ...

ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ነገርና በጭብጥነት ሊያዝ የሚገባው ነገር ከሳሹ ሊከስ የሚችልበት መብት ያለው እንደሆነ የሚያሳይ ወይም ለተከሳሹ መከላከያ ለመሆን የሚችል ማናቸውም የህግ ወይም የፍሬ ነገር መከራከሪያ ነው።።።

ፍ/ቤቱም ጭብጥ የሚመሰርተው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 248 ላይ በተመለከተው አግባብ ሶስት ነገሮችን መሰረት በማድረግ ሲሆን እነዚህም፦

- ግራ ቀኙ በአቤቱታቸው ላይ የዘረዘሯቸውን ነገሮች መሰረት በማድረግ፣
- ግራ ቀኙ ወይም አንደኛው ተከራካሪ ወገን ያቀረበውን የጽሁፍ ማስረጃ መሰረት በማድረግና/ወይም
- ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን በመጀመሪያው ክሱ ሊሰማ በተቀጠረበት ቀን በሚያደርገው ምርመራ ላይ የተከራካሪ ወገኖቹን መከራከሪያ መሰረት በማድረግ ይሆናል።

የቀጠለ...

ፍ/ቤቱ እነዚህን ነገሮች ሲመረምር ማናቸውም ለጉዳዩ አግባብ ያለው ፍሬ ነገር በአንዱ ተከራካሪ ወገን የሚታመንበት ሆኖ በሌላኛው ተከራካሪ ወገን የተካደ ከሆነ በተለየ ራሱን የቻለ አንድ ጭብጥ በማድረግ እንደ አንድ ጭብጥ የሚይዝ እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 247(3) ላይ ተደንግጓል። በዚሁ አግባብ ግራ ቀኙ የሚለያዩባቸውን ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ነገሮች እየመረመረ እንደብዛታቸው የተለያዩ ጭብጦችን ይመሰርታል።

የቀጠለ...

ለ. ፍ/ቤቱ በጭብጥ ምስረታ ጊዜ የፍርድ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችልባቸው ሁኔታዎች

ፍ/ቤቱ በያዘው ጉዳይ ላይ ጭብጥ በሚመሰረትበት ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ ክርክሩን መስማትና ምስክሮችን መመርመር ሳያስፈልገው የፍርድ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችልባቸው ሁኔታዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ላይ ተመልክተው ይገኛሉ። ከነዚህም መካከል የመጀመሪያው ሁኔታ፦-

- በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 254(1) ላይ የተመለከተው ሲሆን ግራ ቀኙ የመጀመሪያው ደረጃ መቃወሚያ ከተሰማና ጉዳዩ ከተጣራ በኋላ ተከራካሪዎቹ ወገኖች በሕጉም ሆነ በፍሬ ነገሩ የሚያከራክራቸው ወይም የሚለያዩበት ጉዳይ ያለመኖሩን ፍርድ ቤቱ የተገነዘበው እንደሆነ በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ነገሩን በፍርድ ለመወሰን የሚችልበት አግባብ ነው።

የቀጠለ...

በመሆኑም ግራ ቀኙ በአከራካሪው ጉዳይ ላይ ያልተለያዩ ከሆነ ፍ/ቤቱ ጭብጥ መስርቶ ክርክር እንዲደረግ የሚያበቃ ምክንያት የሌለው በመሆኑ ጉዳዩን በፍርድ መጨረስ ይኖርበታል።

- ከዚህም በተጨማሪ በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (2) አግባብ ተከሳሾቹ ከአንድ በላይ በሆኑበትና ከእነርሱም መካከል አንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑት ከከሳሹ ጋር የሚያከራክረው የሕግም ሆነ የፍሬ ነገር የሌለ እንደሆነ በተከሳሹ/ሾቹ ላይ ተገቢ ነው የሚለውን ውሳኔ ፍ/ቤቱ የሚሰጥ ይሆናል። በዚህም መሰረት ተከሳሹ ያላግባብ ተጣምሮ የተከሰሰና ይህንኑ አላግባብ መጣመሩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 39(2) መሰረት መቃወሚያ ያላቀረበ በመሆኑ ከክረክሩ እንዲወጣ ያልተደረገ ተከሳሽ በዚህ አግባብ በፍ/ቤቱ ከክሱ እንዲወጣ የሚደረግ ይሆናል።

የቀጠለ...

- ሌላኛውና ሁለተኛው ሁኔታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 255(1) እና (2) ላይ የተደነገገው ሲሆን በዚህም ድንጋጌ መሰረት፡-

ግራ ቀኙ የተለያዩበት የሕግ ወይም የፍሬ ነገር ያለ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ተገቢ ነው የሚለውን ጭብጥ ከያዘ በኋላ ተከራካሪዎቹ ወገኖች በመጀመሪያው ክርክር ላይ ካቀረቡት በቀር ሌላ ተጨማሪ ሙግት ወይም ሌላ ማስረጃ ማስቀረብና መመርመር የማያስፈልግ መሆኑን ሲረዳውና በመጀመሪያ በቀረበው ክርክርና ማስረጃ ብቻ የፍርድ ውሳኔ ቢሰጥ ትክክለኛውን ፍትሕ የማያጓድል መሆኑን የተረዳው እንደሆነ ወዲያውኑ ፍርድ የሚሰጥ ይሆናል።

የቀጠለ...

ይህም የሚሆነው ለክርክር የቀረበው ጉዳይ በተለየ ማስረጃ ብቻ ሊረጋገጥ የሚገባው እንደሆነ በሕግ የተደነገገ ሲሆን ነው። ይህንንም በምሳሌ ብንመለከት ከአምስት መቶ ብር በላይ የሆነ የብድር ውል ሊረጋገጥ የሚገባው በጽሁፍ፣ በፍ/ቤት በሚደረግ የእምነት ቃል ወይም በቃለ-መህላ ማስረጃ ብቻ እንደሆነ በፍትሐብሔር ሕጉ ቁጥር 2472(1) ላይ ተመልክቷል። በዚህም መሰረት ተከሳሹ ያበደርኩትን 2,000 ብር ይመልስልኝ በሚል ክስ ያቀረበ ከሳሽ ይህንኑ ለማስረዳት የሰው ምስክር ዘርዝሮ ቢያቀርብ ፍ/ቤቱ የቀረበለት ጉዳይ በሰው ምስክር ሊረጋገጥ የማይችል በመሆኑ ክሱን ውድቅ በማድረግ ፍርድ ሊሰጥ ይገባል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 247(4) ላይ የተመለከተው ሊታይ የሚገባው ነው። በዚህ ድንጋጌ መሰረት ባንድ ክስ ውስጥ የተያዘው ጭብጥ ለየራሱ ፍሬ ነገርንና ሕግን የሚመለከት በሆነ ጊዜ ፍርድ ቤቱ የሕጉን ጥያቄ በመከተል ክሱን በከፊል ወይም በሙሉ ለመወሰን የሚችል ሲሆን በመጀመሪያ በሕግ ጉዳይ ለተያዙት ጭብጦች ውሳኔ መስጠት አለበት።

የቀጠለ...

እንዲሁም ፍ/ቤቱ ተገቢ ሆኖ ሲያገኘውም በሕግ ረገድ የተያዙትን ጭብጦች እስኪወስን ድረስ በፍሬ ነገር የተያዘውን ጭብጥ በቀጠሮ ሊያቆየው ይችላል።

ለምሳሌ ፍ/ቤቱ የያዛቸው ጭብጦች ውል አለ የለም እንዲሁም ውሉ ባለመፈጸሙ የደረሰ ጉዳት አለ የለም የሚሉ ቢሆኑ በፍሬ ነገር ጭብጥነት የተያዘውን ውሉ ባለመፈጸሙ የደረሰ ጉዳት አለ የለም የሚለውን ጭብጥ ወደኋላ በማቆየት በመጀመሪያ ውል አለ የለም በሚለው ጭብጥ ላይ ውሳኔ ሊሰጥ የሚችል ይሆናል። ምክንያቱም በሕግ ፊት የሚጸና ውል የለም ከተባለ ውሉ ባለመፈጸሙ ጉዳት ደርሷል አልደረሰም የሚለውን ጭብጥ መመልከቱ አስፈላጊ ስለማይሆን ነው።

የቀጠለ...

ሐ. ጭብጥን ሥለማሻሻል

ፍ/ቤቱ ለክርክሩ አወሳሰን ተገቢ ነው ብሎ ሲያምን በመጀመሪያ የያዘውን ጭብጥ ለማሻሻል ወይም ተጨማሪ ጭብጥ ለመመስረት የሚችል እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ /251 ላይ ተደንግጓል።

ፍ/ቤቱ የመሰረተውን ጭብጥ ለማሻሻል የግድ የሚሉ ሁኔታዎች በክርክሩ ሂደት ሊገጥሙት ይችላሉ።

ለምሳሌ ብንመለከት የክስና/ወይም የመልስ አቤቱታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 91(1) መሰረት የተሻሻሉ ከሆኑ ወይም

ከጭብጥ ምስረታ በኋላ ባለው የክርክሩ ሂደት ተከሳሹ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 243 አግባብ በከፊል ያመነ እንደሆነ በመጀመሪያ የተያዙትን ጭብጦች የሚለውጥ በመሆኑ ጭብጡን የግድ ማሻሻል የሚያስፈልግ ይሆናል።

የቀጠለ...

ከዚህም በተጨማሪ ፍ/ቤቱ ለነገሩ አወሳሰን አስፈላጊ ያልሆነ ጭብጥ ሊመሰርት ይችላል። እንዲህ አይነቱ በስህተት የተመሰረተ ጭብጥ ከፍርድ በፊት ሊሰረዝ የሚገባ እንደሆነ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 251(2) ይደነግጋል። በመሆኑም ፍርድ ሊሰጥ የሚገባው ለነገሩ አወሳሰን አስፈላጊ በሆኑ ጭብጦች ላይ መሰረት በማድረግ እንደሆነና ለዚሁ ጉዳይ አወሳሰን አስፈላጊ ያልሆኑትን ጭብጦች እንዳሉ ከመተው ፍ/ቤቱ ሊሰርዛቸው የሚገባ እንደሆነ ነው።

ክፍል አራት

ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ እንደገና ስለሚከለስበት አግባብ

በሥነ-ሥርዓት ሕጉ በአንድ ፍ/ቤት የተሰጠን ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ ለመከለስ የሚቻልባቸው የተለያዩ ሁኔታዎች ተመልክተው ይገኛሉ። እነዚህንም ሁኔታዎች በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍሎ መመልከት ይቻላል።

- የመጀመሪያውና መደበኛው አንድ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ ለማሳረም የሚቻለው የይግባኝ ስርዐቱን ጠብቆ በይግባኝ ሲሆን፣
- ሌላኛውና ሁለተኛው አንድ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ ለማሳረም የሚቻለው በልዩ ሁኔታዎች በራሱ ውሳኔውን፣ ብይኑን ወይም ትዕዛዙን በሰጠው ፍ/ቤት ነው።

ከእነዚህ ሁኔታዎች መካከል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 74 እና 78 የተመለከቱት ሁኔታዎች በክፍል ሁለት የተዳሰሱ በመሆኑ በዚህ ክፍል ሌሎች በሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የምንመለከት ይሆናል።

የቀጠለ...

4.1 ዳኝነት እንደገና እንዲታይ አቤቱታ ስለሚቀርብበት ሁኔታ

እንድ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ በተከራካሪ ወገኖች አመልካችነት እንዲከለስ ለማድረግ የሚቻልበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 6(1) ላይ ተመልክቷል።

በዚህ ድንጋጌ መሰረት ማናቸውም ሰው ይግባኝ ሊቀርብበት በሚችል ፍርድ ወይም ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ላይ ቅሬታውን አቅርቦ ከማሰማቱ በፊት ወይም ይግባኝ ለማቅረብ ያልተፈቀደበት ፍርድ ወይም ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ የተሰጠበት እንደሆነና ይኄው የመጨረሻው ፍርድ ወይም ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ የተሰጠው በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበውን ሰነድ ወይም ሐሰተኛ የምስክርነት ቃልን ወይም መደለያን ወይም ወንጀል ጠቀስ የሆነ ተግባርን መሠረት በማድረግ ሲሆንና አቤቱታ አቅራቢውም ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት አስፈላጊውን ትጋት አድርጐ ለማወቅ ያለመቻሉን ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ እንዲሁም እነዚህ ሁኔታዎች በፍ/ቤቱ ቢታወቁ ኖሮ ለፍርዱ መለወጥ ወይም መሻሻል በቂ ምክንያት ሊሆኑ ይችሉ እንደነበረ ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ ብቻ ፍርዱን ለፈረደው ወይም ትዕዛዙን ወይም ውሳኔውን ለሰጠው ፍርድ ቤት የተወሰነውን ዳኝነት በመክፈል አቤቱታውን ለማቅረብ የሚችል ይሆናል።

የቀጠለ...

በመሆኑም በዚህ ድንጋጌ አግባብ የዳግም ዳኝነት አቤቱታ ለማቅረብ በዋናነት ስድስት ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላት የሚያስፈልጋቸው ይሆናል። እነዚህም፡-

- ዳኝነቱን የሚያቀርበው አቤት ባይ የመጨረሻ ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ በተሰጠው ክርክር ላይ ተሳታፊ የነበረ መሆኑ፤
- የተሰጠው ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ የመጨረሻ መሆኑ፤ የመጨረሻ ውሳኔ የሚለው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 320(1) ምንባብ ለመረዳት እንደሚቻለው ይግባኝ ሊጠየቅበት የሚችል በፍትሐብሔር ፍ/ቤት የተሰጠ ውሳኔ ማለት ነው። ይህ ማለት ግን በይግባኝ ያለቀን ፍርድ አይጨምርም ማለት እንዳልሆነ ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት አንቀጽ 80(3) (ሀ) እና (ለ) ምንባብ መገንዘብ ያስፈልጋል፤
- የተሰጠው ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ በሐሰት ተዘጋጅቶ የቀረበውን ሰነድ ወይም ሐሰተኛ የምስክርነት ቃልን ወይም መደለያን ወይም ወንጀል ጠቀስ የሆነ ተግባርን መሠረት በማድረግ እንደሆነ፤

የቀጠለ...

- አቤት ባዩ ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት አስፈላጊውን ትጋት አድርጎ የቀረበው ማስረጃ ሐሰተኛ ሰነድ ወይም ሐሰተኛ የምስክርነት ቃል ወይም መደለያ ወይም ወንጀል ጠቀስ የሆነ ተግባር የተፈጸመ(በት) መሆኑን ለማወቅ ያለመቻሉን ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ፤
- እነዚህ ሁኔታዎች በፍ/ቤቱ ቢታወቁ ኖሮ ለፍርዱ መለወጥ ወይም መሻሻል በቂ ምክንያት ሊሆኑ ይችሉ እንደነበረ ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ እና
- የተሰጠው ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትእዛዝ ይግባኝ ሊባልበት የሚችል ሆኖ ነገር ግን የይግባኝ ቅሬታ ያልቀረበበት ፍርድ ሲሆን ወይም ይግባኝ ለማቅረብ ያልተፈቀደበት ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ የሆነ እንደሆነ የሚለው ነው።

የቀጠለ...

ይግባኝ ለማቅረብ ያልተፈቀደበት ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትዕዛዝ የሆነ እንደሆነ የሚለው በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ይግባኝ ለማቅረብ የማይፈቀድባቸው ልዩ ልዩ ሁኔታዎችን ለማመልከት ሲሆን ከነዚህም መካከል፡-

- አንቀጽ 6(4)፣ 31(1)፣ 306(1)፣ 320(3)፣ 326(3)፣ 351 የሚጠቀሱ ናቸው።

በእነዚህ ድንጋጌዎች አግባብ የተሰጠው ውሳኔ፣ ብይን ወየም ትዕዛዝ በይግባኝ ሊታረም የሚችል ስላልሆነ ውሳኔው፣ ብይኑ ወይም ትዕዛዙ በአንቀጽ 6(1) በተመለከቱት ሁኔታዎች እንደነገሩ ሁኔታ እንደገና ዳኝነት ሊጠየቅበት የሚችል ይሆናል።

ሌላውና አከራካሪው ነገር **“የይግባኝ ቅሬታውን አቅርቦ ከማሰማቱ በፊት”** የሚለው ምን ማለት ነው? የሚለው ነው።

የቀጠለ...

አንድ ውሳኔ፣ ብይን ወይም ትእዛዝ ይግባኝ የቀረበበት ከሆነ በአንቀጽ 6 (1) ላይ የተመለከተውን ያሟላ ቢሆንኳ ውሳኔውን፣ ብይኑን ወይም ትእዛዝን ለሰጠው ፍ/ቤት በማቅረብ እንደገና ዳኝነት ሊጠየቅበት አይችልም ማለት ነውን?

ሥነ-ሥርዐት ሕጉ **“ማናቸውም ሰው ይግባኝ ሊቀርብበት በሚችል ፍርድ ወይም ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ላይ ቅሬታውን አቅርቦ ከማሰማቱ በፊት”** ሲል ለማለት የፈለገ የሚመስለው አቤት ባዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/6(1)(ሀ) ላይ የተመለከቱትን ወንጀል ጠቀስ ነገሮች ከውሳኔው፣ ከብይኑ ወይም ከትዕዛዙ በኋላ ተረድቶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/345 መሰረት የይግባኝ መሰረት በማድረግ ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አቅርቦ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ተመልክቶ ውሳኔ ሰጥቶበት ከሆነ ያንኑ ተመሳሳይ ነገር የዳግም ዳኝነት ጥያቄ ሊቀርብበት የሚቻል አይሆንም ለማለት እንጂ አንድ ጉዳይ በይግባኝ ከቀረበና በይግባኙ ላይ ውሳኔ ከተሰጠበት በኋላ ለዳግም ዳኝነት መሰረት የሚሆኑት ነገሮች ከተገኙ የዳግም ዳኝነት ጥያቄ ሊቀርብ አይችልም ለማለት አስቦ አይመስልም።

የቀጠለ...

በይግባኝ እስከታየ ድረስ ከይግባኙ ውሳኔ በኋላ ሀሰተኛ በሆነ ማስረጃ ወይም በመደለያ የተሰጠ ውሳኔ መሆኑ ቢረጋገጥም የተሰጠው ውሳኔ የሚጸናና በዳግም ዳኝነት የሚታይ አይሆንም የሚለው የሥነ-ሥርዓት ሕጉ አላማ አይመስልም።

በዚህ ጉዳይ ላይ **የፌዴራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በመጀመሪያ በሰበር መዝገብ ቁጥር 16624 (ቅጽ 2)** ይግባኝ ከቀረበ በኋላ የዳግም ዳኝነት አቤቱታ ለማቅረብ የሚያበቁ ምክንያቶች ቢገኙም የዳግም ዳኝነት ሊቀርብ አይችልም በሚል ውሳኔ ሰጥቶ ነበር።

ይሁንና ይህንኑ ውሳኔውን **በሰበር መዝገብ ቁጥር 43821 (ቅጽ 9)** በሰባት ዳኞች ባስቻለው ችሎት ውሣኔው ሐሰተኛ እና ወንጀል ጠቀስ የሆኑ ተግባሮችን መሰረት በማድረግ የተሰጠ ነው የሚል አቤቱታ እስከቀረበበት እና በቂና አሣማኝ መሆኑን ፍ/ቤቱ እስካመነበት ድረስ ይግባኝ ይባልበትም አይባልበትም ያለልዩነት ሥራ ላይ እንዲውል በሚያስችል ሁኔታ ሲተረጐም ነው የሕጉን ሀሳብ ማሳካት የሚቻለው በሚል በአዲስ ውሳኔ ቀይሮታል።

የቀጠለ...

አቤት ባዩ የዳግም ዳኝነት አቤቱታውን ተገቢውን የዳኝነት አገልግሎት ክፍያ በመክፈል ተገኝቷል የሚለውን አዲስ ማስረጃ ካገኘበት ወይም መኖሩን ካወቀበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ አቤቱታውን ማቅረብ አለበት። የዳግም ዳኝነት አቤቱታ የቀረበለት ፍ/ቤት ከመቀበሉ በፊት የአቤቱታውን ግልባጭ ለባለጋራው በመላክ ባላጋራው አቤቱታው ሊሰማ የማይችልበት መከራከሪያ ካለው እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ሰጥቶ ክርክሩ የሚሰማበትን ቀን ቀጠሮ ይወስናል።

ከዚህም ለመረዳት የሚቻለው የዳግም ዳኝነቱ የሚታየው በመጀመሪያ በቀረበው የዳግም ዳኝነት አቤቱታ ላይ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን መከራከሪያውን ካቀረበ በኋላ እንደሆነ ነው።

ሌላው ከዚሁ ጋር ሊመለስ የሚገባው ጥያቄ የዳግም ዳኝነት አቤቱታ ያስነሳውን ውሳኔ የሰጠው የሰበር ሰሚ ችሎቱ ቢሆን የዳግም ዳኝነቱን ጉዳይ ሊያስተናግድ የሚገባው በየትኛው እርከን ላይ ያለው ፍ/ቤት ነው? የሚለው ነው።

የቀጠለ...

በክልሎችም ሆነ በፌዴራል ፍ/ቤቶች ውስጥ የሰበር ስርዓት የተዘረጋበት ዓይነተኛ ዓላማ አንድ ወጥ የሕግ አተረጓጎም ስርዓትን ለማስፈን ይቻል ዘንድ በመጨረሻ ውሳኔዎች ላይ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተትን ማረም ስለመሆኑ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ.ሕገ መንግስት በአንቀጽ 80(3)(ሀ) እና (ለ)፣ በብ/ክ/መንግስታት ሕገ መንግስቶች እንዲሁም በፌዴራልና በክልሎች ዝርዝር ሕጎች በግልጽ የተመለከተ ነው።

የዳግም ዳኝነት ጥያቄን የሚያስተናግድ ፍ/ቤት ደግሞ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች የማጣራት እና የግራ ቀኙን ማስረጃ የመመዘን ተግባራትን ማከናወን የሚጠበቅበት መሆኑን ከአንቀጽ 6 ይዘት ለመገንዘብ ይቻላል። ይህም አግባብነት ባላቸው የስረ-ነገር እና የስነ ስርዓት ሕጎች መሰረት ፍሬ ነገርን የማጣራት እና ማስረጃን የመመዘን ስልጣን የተሰጠው ለመጀመሪያ ደረጃ እና ለይ/ሰሚ ፍ/ቤቶች መሆኑን እና በዚህ ረገድ ለሰበር ችሎቶች የተሰጠ ስልጣን አለመኖሩን መገንዘብ የሚያስችል ነው።

የቀጠለ...

በመሆኑም በዚህ ጉዳይ ላይ የፌደራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ/ 93137 (ቅጽ 15) የተከራካሪ ወገኖችን የይግባኝ መብት እንዳያጣብብ በማለት በአንቀጽ 6 መሰረት የሚቀርብ የዳግም ዳኝነት አቤቱታ ሊቀርብ የሚገባው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ተመልክቶ ውሳኔ ለመስጠት ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት መሆን እንዳለበት ውሳኔ ሠጥቷል።

የቀጠለ...

4.2 መቃወሚያ ሊያቀርቡ ስለሚችሉ ተከራካሪ ወገኖች

በአንድ ፍ/ቤት የተሰጠ ውሳኔ ላይ በምን አይነት ሁኔታ፣ መቼና ማን መቃወሚያ በማቅረብ የተሰጠው ውሳኔ ተነስቶ እንደገና ክርክር ተደርጎ ውሳኔ ሊሰጥበት የሚቻልበት አግባብ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 358 ላይ ተመልክቷል።

ድንጋጌውም “በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወይም በክርክሩ ውስጥ ለመግባት የሚችልና እንዲሁም ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማናቸውም ሰው ራሱ ወይም ጠበቃው ወይም ነገረ-ፈጁ ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት መቃወሚያውን ለማቅረብ ይችላል” በሚል የተቀመጠ ነው።

የቀጠለ...

ከዚህም ለመረዳት የሚቻለው መቃወሚያ በማቅረብ ዳኝነት ሊከለስ የሚችልበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 6 ከተመለከትነው የዳግም ዳኝነት አቤቱታ በዋናነት የሚለይበት መቃወሚያ አቅራቢው ተካፋይ ባልሆነበት በአንድ ክርክር የተሰጠ ውሳኔ መብቱን ወይም ጥቅሙን የነካበት መሆኑ እንዲሁም መቃወሚያውን ለማቅረብ የሚችለው ፍርዱ ከመፈጸሙ በፊት መሆኑ የሚሉት ቅድመ-ሁኔታዎች ናቸው።

በድንጋጌው **“በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወይም በክርክሩ ውስጥ ለመግባት የሚችል”** የሚለው አገላለጽ የግድ በአንድ ክርክር ተካፋይ መሆን የሚገባው ተከራካሪ ወገንን የሚመለከት እንደሆነ የሚያስረግጥ ነው።

እንደዚህ አይነት ተከራካሪ ወገን ከውሳኔ በፊት ወደ አንድ ክርክር ሊገባ የሚችልባቸው ሁኔታዎች በሥነ-ሥርዓት ሕጉ ተደንግገው እንደሚገኙ የግድ መጣመር ስላለባቸው ተከራካሪ ወገኖች በተመለከትነው ክፍል ተመልክተናል። ከነዚህም ሁኔታዎች መካከል የመጀመሪያው፡-

የቀጠለ...

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 358 መሰረት ከሚቀርብ የመቃወሚያ አቤቱታ ጋር በተያያዘ የተለያዩ ጥያቄዎች የሚነሱ ሲሆን ከነዚህም መካከል፦

እንድ ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር መብቱን ወይም ጥቅሙን የሚነካበት ፍርድ የተሠጠበት ሰው በተሰጠው ፍርድ ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 358 መሰረት መቃወሚ ሳያቀርብ ፍርዱ ቢፈጸም በመብቱ ላይ ምን ውጤት ያስከትላል?

እንዲሁም ይህንኑ ፍርድ የሰጠው የሰበር ሰሚ ችሎቱ ቢሆንና ፍርዱ ከመፈጸሙ በፊት መቃወሚያውን ለማቅረብ ቢፈልግ ለየትኛው ፍ/ቤት ማቅረብ ይኖርበታል?

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 358 በምን አይነት ጉዳዮችና ተከራካሪ ወገኖች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ነጥቦች የፌደራል ሰበር ሰሚ ችሎት ከሰጣቸው ውሳኔዎች ጋር በአጭሩ ለመመልከት እንሞክራለን።

የቀጠለ...

አንድ ሰው በሚመለከተው ጉዳይ ላይ ክርክር እየተደረገ መሆኑን ሳይረዳ ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ቢሰጥና ይኸው ውሳኔ ከተፈጸመ በኋላ መብቱን የነካ ውሳኔ እንደተሰጠ ቢያውቅ ውሳኔውን ለማሳረም የሚችልበት አግባብ ይኖራልን? የሚለውን ጥያቄ በተመለከተ ህጉ በግልጽ የሚደነግገው ነገር የለም።

በመሆኑም በዚህ ረገድ የህጉ ሀሳብ ምን እንደሆነ ለማወቅና በአግባቡ ጥያቄውን ለመመለስ ህጉን በጥንቃቄ መመርመር ያስፈልጋል። የስነ-ስርዓት ህጉን የተለያዩ ድንጋጌዎችን ስንመለከት፣ በአንድ የክስ ምክንያት (cause of action) በጣም ውስን ከሆኑና በግልጽ በህጉ ከተመለከቱ ልዩ ሁኔታዎች ውጪ፣ ከአንድ በላይ የሆነ ክስ እንዲኖር የሚፈቅድ እንዳልሆነ ለመረዳት ይቻላል።

የቀጠለ...

ከዚህ አኳያ አንዳንድ የህጉን ድንጋጌዎች በአስረጅነት ብንወስድ፣

- በአንቀጽ 216 መሰረት ከሳሽ ክሱን ለማቅረብ ምክንያት የሆኑትን ነገሮች ሁሉ በዚያው የክስ ምክንያት ሁለተኛ ክርክር በማያስነሳ ሁኔታ አጠቃሎ ማቅረብ ያለበት መሆኑን የደነገገበት አግባብ፣
- በአንቀጽ 40(2) መሰረት ፍ/ቤቱ በራሱ አስተያየት ወይም በተከራካሪ ወገኖች አሳሳቢነት በከሳሽነት ወይም በተከሳሽነት አንድ ሰው ወደ አንድ ክርክር እንዲገባ የሚደረግበት ሁኔታ፣
- በአንቀጽ 41 መሰረት ጉዳዩ ያገባኛል በሚል ወደ አንድ ክርክር ሶስተኛ ወገን ፍ/ቤትን በማስፈቀድ ጣልቃ የሚገባበት አግባብ፣

የቀጠለ...

- ከፍ/ቤት ውሳኔ በኋላ ውሳኔ ያረፈበት ጉዳይ በክርክር ላይ መሆኑን ከውሳኔው በፊት ያላወቀና ውሳኔው መብቱን የነካበት ሰው የተሰጠው ውሳኔ ከመፈጸሙ በፊት በአንቀጽ 358 መሰረት መቃወሚያ በማቅረብ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይለት ህጉ የዘረጋው መንገድ፣
- እንዲሁም በአንቀጽ 212 መሰረት ደግሞ ማንኛውም አይነት ስነ-ስርዓታዊ ግድፈት የሚጸና ውሳኔ ከመስጠት እንደማያግድ የደነገገበት አኳኋን የህጉ ሀሳብ ለአንድ የክስ ምክንያት አንድ ክስ መቅረብ ያለበት መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው።

የቀጠለ...

በዚህ ጉዳይ ላይ የፌደራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ሁለት የተለያዩ ውሳኔዎችን የሰጠ ሲሆን የመጀመሪያው ውሳኔ **በቅጽ 12 በሰ/መ/ቁ 50835** በሰጠው ውሳኔ ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር መብቱን ወይም ጥቅሙን የነካበት ውሳኔ የተሰጠበት ሰው የተሰጠው ፍርድ የተፈጸመ እንደሆነ በፍ/ሥ/;ሥ/ሕ/ቁ/ 455 መሰረት አዲስ ክስ በማቅረብ መብቱን ከማስከበር የሚከለክለው ነገር የለም በሚል ውሳኔ ሰጥቷል።

የዚህን ውሳኔ አግባብነት ለማይት የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ቁጥር 358፣ 421፣ 446/47 እንዲሁም 455 ድንጋጌዎች አለማና መንፈስ መመልከቱ ጠቃሚ ይሆናል።

የቀጠለ...

ክፍ ብለን ለመመልከት እንደሞከርነው መቃወሚያ ለማቅረብ መብት ያለው ሰው ውሳኔ ያረፈበት ጉዳይ የክስ ምክንያት የሚመለከተው እንደሆነና የተሰጠውም ፍርድ መብቱን የሚነካበት ሆኖ ሲገኝ ነው።

- ከዚህ በተለየ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 421፣ 446/47 እንዲሁም 455 ግን በተመሳሳይ የሚመለከቱት በአከራካሪው ጉዳይ የተሰጠው ውሳኔ መብታቸውን የሚነካ ሳይሆን ይህንኑ የተሰጠውን ውሳኔ ለማስፈጸም ሲባል በተከበረው ወይም በተያዘው ንብረት ላይ የቀዳሚነት መብት አለኝ በሚል፣ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 418 መሰረት የቀረበ መቃወሚያ ውድቅ በሚሆንበት ጊዜ መቃወሚያው ውድቅ የተደረገበት ሰው መቃወሚያ ባቀረበበት ጉዳይ ላይ አዲስ ክስ በማቅረብ መብቱን ለማስከበር የሚችል መሆኑን የተደነገገበት (421)፣
- በአፈጻጸም እንዲሸጥ ጨረታ ወጥቶ የተሸጠ ንብረት ላይ በአግባቡ ሽያጩ አልተደረገም በሚል ሽያጩ በተፈጸመ በ2 ወር ጊዜ ውስጥ መቃወሚያ የሚቀርብበት አግባብ (446/447)፣

የቀጠለ...

- እንዲሁም በአፈጻጸም የተሸጠ ንብረት ገዢው እንዲረከብ በሚል በሚሰጥ የፍ/ቤት ትዕዛዝ ላይ እንዲረከብ በተባለው ንብረት ላይ መብት አለኝ የሚል ሰው ይህንኑ መብቱን በአዲስ ክስ ለማስከበር የሚችል እንደሆነ (455) የደነገገበት ሁኔታን የሚመለከቱ ናቸው።

ከነዚህ ድንጋጌዎች የቁጥር 455"ን" ድንጋጌ ጨምሮ ፍርድ ባረፈበት በዋናው ጉዳይ ላይ መብት የለላቸው ሰዎች ሆነው ነገር ግን በአፈጻጸም ለፍርዱ ማስፈጸሚያ በሚል ንብረታቸው የተያዘባቸውን ሰዎች የሚመለከቱ እንደሆነ ነው። ከዚህ አንጻር ከላይ የተጠቀሰው የፌደራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ ቀደም ሲል በንብረቱ ላይ ክርክር ተደርጎ ፍርድ ተሰጥቶበትና ፍርዱም ተፈጽሞ ባለበት ሁኔታ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ በአንቀጽ 455 መሰረት አዲስ ክስ በማቅረብ መብቱን ማስከበር የሚችል ይሆናል ብሎ ውሳኔ መስጠቱ ከላይ ለመመልከት እንደሞከርነው የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 455"ን" አላማ ያገናዘበ ነው ለማለት የሚያስችል አይደለም።

የቀጠለ...

ከዚህም በተጨማሪ አንድ የፍ/ቤት ውሳኔ መብቱን የሚነካበት ሰው ውሳኔ መሰጠቱን ባለማወቅ ወይም በሌላ ምክንያት በአንቀጽ 358 መሰረት መቃወሚያውን ሳያቀርብ ውሳኔው የተፈጸመበት በመሆኑ መብቱን ለማስከበር አዲስ ክስ ያቅርብ ቢባል የፍ/ቤቶችን ጫና ከመጨመሩም በላይ አንቀጽ 358"ን" ትርጉም አልባ የሚያደርግ በመሆኑ የሰበሩ ውሳኔ የሥነ-ሥርዓት ሕጉን ጠብቆ የተሠጠ ነው ለማለት የሚያስቸግር ነው።

ከዚህ ውሳኔ በተለየ **በቅጽ 13 በሰ/መ/ቁ/ 67127** በተመሳሳይ ጉዳይ አንድ ሰው ባልተካፈልኩበት ክርክር የተሰጠ ፍርድ መብቴን ወይም ጥቅሜን ይጎዳል በሚል የተሰጠውን ፍርድ ወደ ጐን በማለት በሌላ ጊዜ በሚሰጥ አዲስ ፍርድ እንዲቀየር ለማድረግ የሚያስችል የህግ አግባብ የለም በሚል ውሳኔ ሰጥቷል። ይህ ውሳኔ ቀደም ብለን ከተመለከተነው ውሳኔ ይልቅ የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 358"ን" አላማ ያገናዘበ እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል።

የቀጠለ...

በመሆኑም ከላይ በመነሻነት በተነሳው ሁኔታ በተመለከተው ሰው ላይ በግልጽ በህጉ ባይመለከትም በትርጉም ደረጃ በፍርድ የማለቅ መርህ ተፈጻሚ የሚሆንበት ይሆናል።

በአንድ ክርክር ተካፋይ ባልሆነበት መብቱን ወይም ጥቅሙን የነካበት ውሳኔ የተሰጠበት አንድ ሰው በአዲስ ክስ መብቱን ወይም ጥቅሙን የሚያስከብርበት ልዩ ሁኔታ መብቱን ወይም ጥቅሙን የነካበት ውሳኔ የሰጠው ፍ/ቤት የሰበር ሰሚ ችሎቱ ከሆነ ነው። ይህም በተለይ ሀገራችን ካወጣችው የ1987''ቱ" የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስትና እርሱን ተከትለው በወጡት የክልሎች ህገ መንግስታት እንዲሁም ሌሎች ዝርዝር ህጎች የሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቋቋም በመደረጉ ምክንያት የመጣ ነው።

የቀጠለ...

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገመንግስት አንቀጽ 80(3)(ሀ) እና (ለ) ላይ እንደተመለከተው የፌደራልም ሆነ የክልል ሰበር ሰሚ ችሎቶች መሰረታዊ የሆኑ የሕግ ስህተቶችን የማረም ሥልጣን ብቻ ነው ያላቸው። በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 358 መሰረት የሚቀርብ የመቃወሚያ አቤቱታ ደግሞ የማስረጃ ምርመራና ምዘና የሚያካተት በመሆኑ የሰበር ሰሚ ችሎቱ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተትን ከማረም ባለፈ እንዲህ አይነቱን የማስረጃ ምርመራና ምዘና ለማድረግ ሥልጣን የሌለው በመሆኑ በሰበር ሰሚ ችሎቱ ውሳኔ መብቱ የተነካበት ሰው ለሰበር ሰሚ ችሎቱ መቃወሚያውን ሊያቀርብ የሚችልበት አግባብ አይኖርም።

የቀጠለ...

ከዚህ ጋር በተያያዘ የፌደራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት **በቅጽ 13 በሰ/መ/ቁ/ 31264 እንዲሁም በቅጽ 19 በሰ/መ/ቁ 102056** ተመሳሳይነት ያላቸው ሁለት ውሳኔዎችን ሰጥቷል። በእነዚህም ውሳኔዎች መሰረት በሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ መብቱ የተነካበት ሰው መብቴን ተጋፍቷል በሚለው ሰው ላይ በስሙ ቀጥታ ክስ በመመስረት መብቱን ከሚያስከብር በስተቀር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 358 አግባብ መቃወሚያውን ለሰበር ችሎቱ ሊያቀር አይችልም የሚል ነው።

ከዚህም በተጨማሪ ቀደም ብሎ ባለቀው ክርክር የተሠጠው ፍርድ ከተፈጸመ በኋላ ቀደም ሲል በመከራከሪያነት ከተነሳው የመብት አይነት የተለየ የመብት መከራከሪያ ያለው ሰው በዚያው ፍርድ አርፎበት በተፈጸመው ጉዳይ አዲስ ክስ በማቅረብ መብቱን ለማስከበር እንደሚችል የፌደራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት **በሰ/መ/ቁ/ 114930** በተለይም ከመሬት ጋር አያይዞ ውሳኔ ሰጥቷል።

የቀጠለ...

በዚህም ውሳኔ መሰረት 2 ግለሰቦች በአንድ መሬት የይዞታ መብት ላይ ሲከራከሩ ቆይተው ፍ/ቤቱ የመሬቱ ይዞታ ለአንደኛው ሰው ይገባል በሚል ውሳኔ ሰጥቶ ይሄው ውሳኔ ከተፈጸመ በኋላ የአካባቢ ጥበቃና መሬት አስተዳደር በዚሁ በፍርድ ባለቀው መሬት ላይ አዲስ ክስ በማቅረብ መብቱን ለማስከበር የሚችል እንደሆነ ነው።

ምክንያቱም የአካባቢ ጥበቃና መሬት አስተዳደር የሚያነሳው መከራከሪያ ቀደም ብሎ በግለሰቦች መካከል የተነሳውን የይዞታ ጥያቄ ሳይሆን የባለቤትነት ጥያቄን መሰረት በማድረግ በመሆኑ ነው።

የቀጠለ...

ሌላው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 358 ጋር በተያያዘ ሊነሳ የሚገባው ነጥብ ድንጋጌውን ጠቅሶ መቃወሚያ ለማቅረብ የማይቻልባቸው ሁኔታዎች ምን አይነት ሁኔታዎች ናቸው? የሚለው ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ በመጀመሪያ ደረጃ ድንጋጌው ተፈጻሚነት የማይኖረው መብቱን ወይም ጥቅሙን የሚነካ ውሳኔ ሊያሰጥ የሚችል ክርክር በአንድ ፍ/ቤት እየተካሄደ መሆኑን እያወቀ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በሥነ-ሥርዓቱ አግባብ ወደ አንድ ክርክር ባልገባ ተከራካሪ ላይ ነው። ይህንንም በምሳሌ ለመመልከት ያህል በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 40(2) በግልጽ ከፍቃዱ ውጪ አንድ ሰው በአንድ ክርክር በከሳሽነት እንዲገባ እንደማይገደድ ተደንግጓል። በዚህ አግባብ በከሳሽነት ወደአንድ ክርክር እንዲገባ ፍ/ቤት ያሳሰበው ሰው ወደአንድ ክርክር በከሳሽነት እንዲገባ ያለመገደድ መብቱን በመጠቀም ወደ ክርክሩ ባልገባበት ሁኔታ ፍ/ቤቱ በሌለሁበት የሰጠው ውሳኔ መብቴን የሚነካ ነው በሚል በህጉ አንቀጽ 358 መሰረት ጉዳዩ ባለሁበት ተሰምቶ ይወሰንልኝ በሚል ቢያመለክት ማመልከቻው ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባ አይሆንም።

የቀጠለ...

በዚህ አይነቱ ሁኔታ መቃወሚያ በማቅረብ ክሱ እንደገና እንዲታይለት መፍቀድ ድንጋጌው የተቀረጸበት አላማ ሊሆን እንደማይችል ከፍ/ቤት ኢኮኖሚያዊነትና ቀልጣፋ የፍትሃብሄር የፍትህ ስርዓት ማሳካት ከሚሉት የህጉ አላማዎች ለመገንዘብ ይቻላል። በዚህም አግባብ የፊደራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት **በቅጽ 12 በሰ/መ/ቁ/ 56795** በሰጠው ውሳኔ አንድ ክርክር መጀመሩን ያወቀ ወገን የክርክሩን ውጤት ጠብቆ መብቱን የሚነካበት ሆኖ ባገኘው ጊዜ ከውሣኔው በኋላ የሚያቀርበው አቤቱታ በፍትሐብሄር ስነ-ስርዓት ህጉ አንቀጽ 358 መሰረት ተቀባይነት እንደማይኖረው አስገዳጅ ትርጉም ሰጥቷል።

የቀጠለ...

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 358 ተፈጻሚነት የማይኖረው ለፍ/ቤት ማረጋገጫ እንዲሰጥ በቀረበ ጥያቄ ላይ በሚሰጥ ውሳኔ ወይም ትእዛዝ ላይ ነው። እንዲህ አይነት ማረጋገጫ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ ቁጥር 300 እና ተከታዮቹ የሚጠየቅ ሲሆን በዚህ አግባብ ፍ/ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ ላይ መቃወሚያ አለኝ በሚል አቤቱታ ለማቅረብ የሚቻል አይሆንም።

ምክንያቱም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 358 የሚመለከተው ግራ ቀኙ ተከራክረውበት መብትን ወይም ግዴታን ያስከተለ ውሳኔ በተሰጠበት ጉዳይ መብቴ ወይም ጥቅሜ ተነክቷል የሚል ሰው መቃወሚያ በማቅረብ መብቱን የሚያስከብርበት ድንጋጌ በመሆኑ ነው። በዚህም አግባብ የፌደራሉ ሰበር ሰሚ ችሎት **በሰ/መ/ቁ 79871 (ቅጽ 15)** ላይ የወራሽነት ማረጋገጫን በተመለከተ ወራሽነትን በማረጋገጥ በተሰጠ የወራሽነት ማስረጃ ላይ መብቴን ወይም ጥቅሜን ይነካል በሚል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 መሠረት የሚቀርብ የመቃወሚያ አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ሥለመሆኑ እና ተረጋግጦ የተሰጠውን ማስረጃ በሌላ ክርክር መቃወም የሚችል እንደሆነ ውሳኔ ሰጥቷል።

የቀጠለ...

4.3 መሰረታዊ የሥነ-ሥርዐት ግድፈትና ሊታረም የሚገባበት አግባብ

ከፍ ብለን ከተመለከትናቸው አንድ ፍርድ ከተሠጠ በኋላ እንደገና ሊታይ ከሚችልባቸው ሁለት ሁኔታዎች በተለየ ከፍርድ በፊት የሚፈጸሙ የሥነ-ሥርዓት ግድፈቶች ሊታረሙ የሚችሉበት አግባብ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ ከቁጥር 207-211 ባሉት ድንጋጌዎች ተመልክቶ ይገኛል።

በዚህ አግባብ የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ሊታረም የሚችልበት ሁኔታ በመርህ ደረጃ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 207 ላይ እንደተደነገገው “በሕግ ተለይቶ ካልተደነገገ ወይም ፍርድ ቤቱ በሌላ አኳኋን እንዲፈጸም ልዩ ትእዛዝ ካልሰጠ በቀር በዚህ ሕግ የተመለከቱትን ውሣኔዎች ወይም በውሣኔዎቹ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ባለመፈጸም ከሥነ-ሥርዓት ውጭ የሆነ ክስ ሲቀርብ ወይም በክሱ ውስጥ ከደንብ ውጪ የሆነ ተግባር ሲፈጸም ከተከራካሪዎቹ ወገኖች አንዱ ባመለከተ ጊዜ ወይም ፍርድ ቤቱ በራሱ ሥልጣን ይህ ከሥነ-ሥርዓት ውጪ የቀረበው ክስ በከፊል ወይም በሙሉ እንዲሠረዝ ወይም ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ በዚህም ምክንያት ስለሚደርሰው ኪሣራና ስለሌላውም ወጪ ተስማሚ መስሎ የታየውን ትእዛዝ ይሰጣል” በሚል ተደንግጓል።

የቀጠለ...

በዚህ ድንጋጌ መሰረትም ከሥነ-ሥርዓት ውጭ የሆነ ክስ ሲቀርብ ወይም በክሱ ውስጥ ከደንብ ውጪ የሆነ ተግባር ሲፈጸም ከተከራካሪ ወገኖች መካከል አንዱ ባመለከተ ጊዜ ወይም ፍ/ቤቱ በራሱ ሥልጣን ከሥነ-ሥርዓት ውጪ የቀረበውን ክስ ወይም በክሱ ውስጥ ከደንብ ውጪ የተፈጸመውን ተግባር እንደነገሩ ሁኔታ በሁለት መልኩ ለማረም የሚችል ይሆናል። ይኼውም ከሥነ-ሥርዓት ውጪ የቀረበው ክስ በከፊል ወይም በሙሉ እንዲሠረዝ ወይም ክሱ ተሻሽሎ እንዲቀርብ በማድረግ ይሆናል። ለምሳሌ ብንመለከት ተከሳሽ በቀረረበት ክስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቦ ነገር ግን ፍ/ቤቱ የቀረበው መቃወሚያ ላይ ምንም ሳይል ጭብጥ በመመስረት ወደማስረጃ መስማት ያለፈ እንደሆነና ተከሳሽ ለፍ/ቤቱ ባቀረበው መቃወሚ ላይ ብይን ይስጥልኝ በሚል ቢያመለክት፤

የቀጠለ...

- ፍ/ቤቱ በመቃወሚያው መሰረት ክሱን የሚያዘጋ ሆኖ ካገኘው የጭብጥ ምስረታውንና የማስረጃ መስማቱን የክርክር ሂደት ሙሉ በሙሉ በመሰረዝ ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚ መዝጋት፤ ወይም
- በመጀመሪያ ደረጃው መቃወሚያ ክሱ የማይዘጋ ሆኖ ካገኘው ይህንኑ መቃወሚያ በብይን ውድቅ በማድረግ ቀደም ሲል የመሰረተውን ጭብጥና ያከናወነውን የማስረጃ መስማት ባለበት እንዲቀጥል ለማድረግ የሚችል ይሆናል።

የቀጠለ...

የሥነ-ሥርዓት ግድፈት አለ በሚል በተከራካሪ ወገኖች የሚቀርብ ማመልከቻ ተቀባይነት እንዲኖረው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 209(3) እና 210(1) መሰረት ሁለት ቅድመ-ሁኔታዎች ተሟልተው መገኘት ይኖርባቸዋል። የመጀመሪያው ቅድመ-ሁኔታ በሕጉ ቁጥር 210(1) (ሀ) ላይ የተመለከተው ሲሆን ይኼውም የሥነ-ሥርዓት ግድፈቱ በሥረ-ነገሩ ላይ የተያዘውን ጭብጥ የሚለውጥ ወይም የሚነካ ሆኖ በአመልካቹ መብት ላይ ማናቸውንም ዓይነት ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ የሚለው ነው። በተለይ **“የተያዘውን ጭብጥ የሚለውጥ ወይም የሚነካ”** የሚለው የሕጉ አገላለጽ በተከራካሪ ወገኖች ሊቀርብ የሚችል የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ሊነሳ የሚችለው ከጭብጥ ምስረታ በኋላ ለሚፈጸም የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ይመስላል።

የቀጠለ...

ይሁንና የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዝኛ ቅጂ “an irregularity has occurred which affects the issue to be decided and has prejudiced or is likely to prejudice the applicant” በሚል የተደነገገ ሲሆን በዚህም ቀደም ሲል በተያዘ ጭብጥ ላይ ሳይሆን ወደፊት ፍ/ቤቱ ሊወስን የሚችለውን ጭብጥ የሚነካ እንደሆነና ይህም የአመልካቹን መብት ሊጎዳ የሚችል እንደሆነ በሚል የተቀመጠ መሆኑን መመልከት ይቻላል። የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ጭብጥ ከተመሰረተ በኋላ ብቻ ሳይሆን ብዙ የሥነ-ሥርዓት ግድፈቶች ከጭብጥ ምስረታ በፊትም ሊፈጸሙና ፍ/ቤቱ ወደፊት ውሳኔ ሊሰጥባቸው የሚችሉ ጭብጦችን በመንካት የአመልካቹን መብት የሚጎዱበት ሁኔታ ሊፈጥሩ እንደሚችሉ በቀላሉ ለመረዳት ይቻላል። በመሆኑም ከሁለቱ ቅጂዎች የእንግሊዝኛው ቅጂ ከዚህ አንጻር በተሻለ የሕጉን ሀሳብ ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን መመልከት ይቻላል።

የቀጠለ...

- ሌላኛውና ሁለተኛው ሊሟላ የሚገባው ቅድመሁኔታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 209 (3) መሰረት ከሥነ-ሥርዓት ውጭ ነው በማለት የሚቀርብ አቤቱታ ሁሉ አመልካቹ ከሥነ-ሥርዓት ውጭ ነው የተባለው ነገር መኖሩን እንደተረዳው ልክ እንደመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ሁሉ በመጀመሪያው ደረጃ ማመልከት ያለበት መሆኑ ነው። በመሆኑም በቶሎ ያልቀረበ የሥነ-ሥርዐት ግድፈት መቃወሚያ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 211 (1) ከተመለከተው ሁኔታ ውጪ ማመልከቻ ተቀባይነት የሚኖረው አይሆንም። የሥነ-ሥርዐት ግድፈት ተፈጽሟል በሚል ማመልከቻ የቀረበለት ፍ/ቤት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 210 (1) ለ ላይ እንደተመለከተው አመልካቹ የሥነ ሥርዓት ጉድለት አለበት የተባለው ነገር መኖሩን እንደተረዳ ወዲያውኑ በነገሩ ላይ ማናቸውንም ዓይነት እርምጃ ያልወሰደ መሆኑን እርምጃ ወስዶ እንደሆነም አለ የተባለውን ጉድለት በመቃወም ያመለከተ መሆኑን ሲያረጋግጥ ትእዛዝ የሰጠበትን ምክንያት በዝርዝር በመግለጽ በዚህ ሕግ በቁጥር 207 የተነገረውን መሠረት በማድረግ አቤቱታውን ተቀብሎ ክፍ ብለን ለመመልከት በሞከርነው አግባብ ተስማሚ መስሎ የታየውን ትእዛዝ ይሰጣል። ከላይ የተመለከትናቸው ቅድመሁኔታዎች ተሟልተው ያልተገኙ እንደሆነ የአመልካቹን ማመልከቻ ውድቅ በማድረግና ማመልከቻ እንዳልቀረበ በመቁጠር ክርክሩ ባለበት የክርክሩ ደረጃ እንዲቀጥል ፍ/ቤቱ ያደርጋል።

- የትዛዝ ይግባኝን በተመለከተ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 211 ላይ የተደነገ ሲሆን በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር (1) መሰረት የሥነ-ሥርዐት ግድፈት አለ በሚል ከላይ በተመለከትነው አግባብ ማመልከቻ ያልቀረበ እንደሆነ ፍ/ቤቱ በሰጠው ፍርድ ወይም ውሳኔ ምክኒያት ካልሆነ በስተቀር በሥነ-ሥርዓት ጉድለት ምክንያት ብቻ የትእዛዝ ይግባኝ ለማቅረብ የሚቻል አይሆንም። ከዚህ በተለየ የሥነ-ሥርዐት ሕጉ ቁጥር 211 (1) የእንግሊዝኛው ቅጂ በስረ-ነገር ስልጣ ረገድ የተፈጸመ የሥነ-ሥርዐት ግድፈት መኖሩን ወዲያውኑ ማመልከቻ ባይቀርብም በየትኛውም የክርክሩ ደረጃ ሊነሳ እንዲሁም ይኄው ግድፈት ማመልከቻ ባይቀርብበትም ይግባኝ ሊባል የሚችልበት እንደሆነ ደንግጓል። ይህም የፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 209 (3) ልዩ ሁኔታ ያደርገዋል።

- ከዚህ ልዩ ሁኔታ ውጪ በተፈጠረ የሥነ-ሥርዐት ግድፈት ማመልከቻ ያልቀረበበት በመሆኑ የይግባኝ ምክኒያት ለመሆን ባይችልም በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 211 (2) እና 182 (2) መሰረት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እንደሥነ-ሥርዐቱ ጉድለት አይነት በሁለት መልኩ የተፈጸመውን የሥነ-ሥርዐት ጉድለት ለማረም የሚችል ይሆና። የመጀመሪያው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተፈጸመን የሥነ-ሥርአት ጉድለት ለማረም የሚችልበት አግባብ ይግባኝ በተባለበት ጉዳይ ላይ የተፈጸመውን ማንኛውንም የሥነ-ሥርዓት ጉድለት በራሱ አስተያየት ሊያርም የሚችልበት ሁኔታ ነው። ይህም በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ፈቃጅነት እንጂ የግድ ሊደረግ ይገባል የማይባል ተግባር ነው።

- ነገር ግን ያጋጠመው የሥነ ሥርዓት ጉድለት ለትክክለኛው ፍርድ አሰጣጥ ተቃራኒ መስሎ የታየው እንደሆነ የተፈረደው ፍርድ እንዳልተፈረደ ሆኖ እንደገና እንዲታይ ትእዛዝ የሚሰጥበት አግባብ ሁለተኛው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኝ በቀረበበት ጉዳይ ላይ የተፈጸመን የሥነ-ሥርዐት ጉድለት የግድ የሚያርምበት የሕግ ግዴታ ነው።
- ከሥነ-ሥርዐት ጉድለት ጋር በተያያዘ ግንዛቤ ሊወሰድበት የሚገባው ነገር የትኛውም አይነት የሥነ-ሥርዐት ጉድለት ቢሆን፣ ለትክክለኛው ፍርድ አሰጣት ተቃራኒ ቢሆንም እንኳ ጉድለቱ ይግባኝ ካልቀረበበት ወይም ይግባኝ ቀርቦበት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የበታቹ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሳኔ እስካጸና ድረስ ውሳኔው የጸና የሚሆን እንደሆነ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 212 ላይ ተደንግጓል። በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ